በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
**ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY**
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
**ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE**
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 507/05

ቀን: 19/11/05 ዓ.ም

ለ: ም/ስራ አስኪያጅ /የተገልጋዮች አገልግሎት ድጋፍ/
ሁሉም የሥራ ሂደት
ገላን ተርሚናል ማስተባበሪያ
በስራ አስኪያጅ ስር ላሉ ቡድኖች
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፤

ከ: ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፤

የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ የዕቃ ማስተላለፍና የበሕር ወደብ አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ የተፈጠረው ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ መመሪያ ቁጥር 2/2006 ሐምሌ 1/2006 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ትግበራ መግባቱን እና በመመሪያው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ተገቢውን እንዲፈፀም በማሳሰብ ገልፆ ጽፎልናል፡፡

በመሆኑም በተፃፈልን መሠረት እንድታውቁት እያሳሰብኩ፤ የደብዳቤው ኮፒ ከዚሁ ሸኚ ጋር የተላከላችሁ መሆኑን እገልፃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3.0/11/07
Ref.No.
ቀን 17 ሐምሌ 2006
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ጉዳዩ፡- <u>የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባሕር ወደብ አገልግሎት ክፍያን መመሪያ ይመለከታል</u>

የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በ9/11/06 በቁጥር ኮ/17/ማጉባ/18/06 በፃፈው ደብዳቤ የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባህር ወደብ አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መንግስት በተፈረመው የወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሠረት ለመተግበር በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰብሳቢነት ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የመንግስት፣ የልማት ድርጅቶች የሙያ ማህበራትን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከጅቡቲ አቻው ጋር ከመደራደር ጀምሮ የተለያዩ ተግባራትን ሲከናወን መቆየቱን ገልፆ የአከፋፈል ሂደቱን በሥርዓት ለመምራት በመመሪያ ደረጃ ሃገራዊ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ፣ መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከሐምሌ 1/2006 ዓ.ም ጀምሮ ጸድቆ ወደ ትግበራ መግባቱን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም የሚመለከታቸው የባለስልጣኑ የስራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች በመመመሪያው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ተገቢውን እንዲፈፀም እያሳሰብን የተላከልንን መመሪያ እና ደብዳቤ 14 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገዛኸኝ
ም/ዋና ዳይሬክተር
ፕሮግራም ዲዛይንና
ልማት ሥራዎች ዘርፍ

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- ለአገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናዜሽን ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ.ቁ. / Tel. 011-466 74 66
ፋክስ / Fax 011-466 82 44
ኢሜል / E-mail erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website WWW.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

## ዋና መ/ቤት

❖ ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ
❖ ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
❖ ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
❖ ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
❖ ለየዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
❖ ለየድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

## ቅ/ጽ ቤቶች

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለአዳማ ገቢዎች ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>አዳማ</u>
- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሚሌ</u>
- ለጐንደር ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ

  <u>ጐንደር</u>
- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>መቀሌ</u>
- ለጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጅጅጋ</u>
- ለድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ድሬዳዋ</u>
- ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ኮምቦልቻ</u>
- ለሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሞጆ</u>
- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሞያሌ</u>
- ለጋላፊ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጋላፊ</u>
- ለጅቡቲ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጅቡቲ</u>

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በትራንስፖርት ሚኒስቴር
የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport
Maritime Affairs Authority

ቁጥር ኀ/1ተ/ህግን/18/11/06
No.

ቀን 09/11 ዓ.ም 06
Date

አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባሕር ወደብ አገልግሎት ክፍያን መመሪያን ይመለከታል፡፡</u>

የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባህር ወደብ አገልግሎት ክፍያን በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መንግሥት በተፈረመው የወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሠረት ለመተግበር በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰብሳቢነት ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የመንግሥት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የሙያ ማኅበራትን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከጅቡቲ አቻው ጋር ከመደራደር ጀምሮ የተለያዩ ተግባራት ሲከናወን መቆየቱ ይታወሳል፡፡

በዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባህር ወደብ አገልግሎት ክፍያ አተገባበርን በተመለከተ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እንዲሁም የአከፋፈል ሂደቱን በሥርዓት ለመምራት በመመሪያ ደረጃ አገራዊ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ በመታመኑ ጥናትን መሠረት ባደረገ መልኩ አገራዊው መመሪያ ተዘጋጅቶ፤ መመሪያ ከሀምሌ 1/2006 ዓ.ም ጀምሮ ጸድቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

በመሆኑም መመሪያዉ ከሐምሌ 1/2006 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ትግበራ የተገባ ስለሆነ ብሔራዊ ባንክም በመመሪያዉ የተሠጠዉን ተግባር እና ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት ለአገራዊዉ መመሪያ ትግበራ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት እያስታወስን የጸደቀዉን መመሪያ የዚህ ደብዳቤ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኀብተን አበራ
ዋና ዳይሬክተር

<u>አባሪ</u>፣ የተጠቀሰው

<u>ግልባጭ</u>

- ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
- በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ
  <u>አዲስ አበባ</u>